በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሰሜን አሜሪካ
ሰንበት ት/ቤቶች አንድነት
The Ethiop'ia Orthodox Tewahedo Church-North America Sunday Schools Union (EOTC-NASSU)
Tel: (630) 660-1850 ~ Fax: (630) 328-7346 ~ P.O. Box 9544 ~ Naperville, IL 60567
URL: http://www.onetewahedo.org ~ e-mail: info@onetewahedo.com

« እስመ ኀበ ሀለዉ ክልኤቱ ወሠለስቱ ጉቡኣን በስምየ ሀየ እሄሉ አነ ማእከሎሙ (ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና።)» ማቴ ፲፰ ፣ ፳

« ትግሁ ወቁሙ በሃይማኖት ተፀነዑ ወጽኑ። ወኩሉ በፍቅር ግበሩ። (ንቁ በሃይማኖት ጽኑ ጎልምሱ ጠንክሩ ሁሉን በፍቅር አድርጉት።)» ፩ ቆሮ ፲፮ ፲፫

*በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ዱ አምላክ...... አሜን።*

ቁጥር ሰ/አ/ሰ/ት/አንድነት/ጉ-ሪፖ01/2000
ቀን 05/06/2000

በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስተደን የሰንበት ተማሪዎች አባላት

**ጉዳዩ:- የስድሰት ወር ሪፖርት ስለመላክ ይመለከታል**

የሰሜን አሜሪካ የሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት ጉባኤ በዓመት ሁለት ግዜ ለማህበሩ አባላት ማህበሩ ሲያከናውናቸው የነበሩ ስራዎችን ሪፖርት ማቅረብ ባለበት ሃላፊነት መሰረት የመጀመሪያውን የሰድስት ወር የሥራ ሪፖርት /ከመስከረም እስከ የካቲት/ ድረስ የተከናወኑ ስራዎችን የያዘ አራት ገጽ አባሪ አድርገን የላክን መሆናችንን በትህትና እናሳውቃለን።

ከመንፈሳዊ ሰላምታ ጋር

ሐምራዊት ጸጋዬ
የማህበሩ ሰብሳቢ

# <u>የሰሜን አሜሪካ የሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት ጉባኤ የስድስት ወር የስራ ሪፖርት</u>

እንደሚታወቀው የሰሜን አሜሪካ የሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት ጉባኤ በዓመት ሁለት ግዜ የማህበሩን የስራ እንቅስቃሴ የሚገልጽ ሪፖርት ለጠቅላላ አባላቱ ማቅረብ እንዳለበት የተወሰነ በመሆኑ የመጀመሪያውን ግማሽ ዓመት ሪፖርት ማለትም ከመስከረም እስከ የካቲት ፳፻፩ ዓ.ም በማህበራችን ሲሰራ የነበሩትንና ሳይከናወኑ የቀሩትን ዝርዝር ስራዎች ከዚህ በታች እናቀርባለን

## ፩ <u>ማህበራችን በመጀመሪያው ስድስት ወራት ካከናወናቸው አንኳር ሥራዎች መካከል</u>

- በዴንቨር ኮሎራዶ በተደረገው በሰባተኛው ጠቅላላ ጉባኤ ወቅት በተጓደሉት የስራ አስፈጻሚ አባላት ምትክ ምርጫ ከተደረገ ግዜ አንስቶ ቀደም ብለው ማህበሩን ሲያገለግሉ ከነበሩት የስራ አስፈጻሚዎች ጋር የስራ ድልድል በማድረግ ሁሉም ስራ አስፈጻሚዎች ሥራቸውን አውቀው ሃላፊነታቸውን እንዲወጡ መመሪያ ተሰጥቷል፡፡
- በ ፳፻፩ ዓ.ም የማህበሩ ሥራ አስፈጻሚዎች ሥራቸውን በትጋና በጥራት እንዲሰሩ ለማድረግ ይቻል ዘንድ በአገልግሎት አቻ ከሆነውና በአገልግሎት ደረጃ ልምድ ካካበተው ከማህበረ ቅዱሳን ጽ/ቤት ጋር የልምድ ልውውጥ ለማድረግ ተችሏል፡፡
- የማህበራችን የመዝሙር ክፍል ተጠሪ ካለበት የስራና የትምህርት ጫና ምክንያት የክፍሉ ሥራ በሚጠበቀው ሁኔታ ባለመከናወኑና በሚፈለገው የአገልግሎት ፍጥነት ውጤት ባለመታየቱ ምክንያት በምትኩ አዲስ ተጠሪ በመወከል የክፍሉ ሥራ እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡
- ማህበሩ እስከ አሁን የነበረው እንቅስቃሴ ሰንበት ትምህርት ቤቶችን ያሳተፈና የሚያንቀሳቅስ አለመሆኑ ማህበሩን በተለያዩ የስራ ክፍፍል ላይ አሉታዊ ተጽዕኖዎች አሳድሯል፤ ስለሆነም በዚህ ዓመት በሰሜን አሜሪካ የሚገኙ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ ሰንበት ት/ቤቶችን የማነቃቃትና የማበረታታት ስራ እንዲሰራ ጥረት ተደርጓል፡፡
- ማህበሩ በዚህ ዓመት በሰሜን አሜሪካ የሚገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ አብያተክርስቲያናት፣አገልጋይ ካህናትና ሰንበት ት/ቤቶችን የያዘ አንድ ወጥ የሆነ ዳሬክተሪ ለማዘጋጀት ባደረገው ጥረት መሠረት ሰባ አምስት በመቶ ያህሉ ተከናውኗል፡፡
- ማህበራችን በዚህ የሪፖርት ወቅት ለማህበሩ የወደፊት አሰራር ይጠቅማሉ ያላቸውን 13 የሚያህሉ አጀንዳዎችን በማዘጋጀት አትላንታ ላይ ሁሉም የስራ አስፈጻሚ አባላት በአካል በመገናኘት ለሶስት ቀን ያህል ውይይት ተደርጓል፡፡በዚሁ የስብሰባ ወቅት ለማህበራችን የወደፊት አሰራር የሚጠቅሙና አባላትን ከማፍራት እንደዚሁም የማህበሩ የወደፊት ዓላማና ራዕይ ምን ሊሆን እንደሚገባ ሰፋ ያለ ግንዛቤና ጠንከር ያለ ማሳሰቢያ በመስጠት ውይይቱ ተቋጭቷል፡፡
- የማህበራችን ሥራ አስፈጻሚዎች አትላንታ ላይ በአካል ተገናኝተው ስብሰባ ባደሩገበት ወቅት ትኩረት በመስጠት ከተወያዩባቸው ጉዳዮች መካከል የወቅቱ የቤተክርስተደን ችግር የሆነውን የአክራሪ ሙስሊሞች እንቅስቃሴ በተመለከተ ሲሆን የአክራሪ ሙስሊሞች እንቅስቃሴ የቤተክርስቲያናችን ከባድ ችግር በመሆኑ ማህበራችን በሚችለው አቅም በሙሉ ሊንቀሳቀስ እንደሚገባ ተወስቷል፡፡በዚህ ዓመት ለአስቸኳይ ግዜ ሥራ የሚውል 2000 ዶላር ከማህበሩ ካዝና ወጪ እንዲሆንና የአክራሪ ሙስሊሞች አንቅስቃሴ በጎላበትና ሰባኪያ ወንጌል ዕጥረት ባለበት አካባቢ መንፈሳዊ ሥራ እንዲሰራበት ወስኗል፡፡
- የአክራሪ ሙስሊሞችን እንቅስቃሴ በተቻለ መጠን በአባላቱና በምዕመናን ዘንድ ግንዛቤ ለመፍጠር ይቻል ዘንድ በማህበሩ ዌብ ሳይት ላይ ጽሁፎች እንዲጻፉና አባላቱ ወቅታዊ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ ጥረት ተደርጓል በተጨማሪም በስምንተኛው ጠቅላላ ጉባኤ ላይ አንድ ሴሚናር በማዘጋጀት የገቢ ማሰባሰቢያ መንገድ ለመፍጠር እንዲቻል ማህበሩ በዝግጅት ላይ ይገኛል፡፡
- ማህበሩ ላለፉት ሰባት ዓመታት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ አብያተክርስቲያናት ውስጥ በሚገኙ ሰንበት ትምህርት ቤቶች ዓመታዊ ጉባኤ በየዓመቱ አካሂዷል፡፡በዚህም ዓመት ለስምንተኛ ግዜ ለሚደረገው ጉባኤ ሰንበት ትምህርት ቤቶች ዓመታዊ ጉበኤ ማስተናገድ ይችሉ ዘንድ የጥሪ ደብዳቤ አውጥቶ የጥሪውን ደብዳቤ ተቀብለው በግዜው መልስ ከሰጡት መካከል የዲሲ ደብረ ምህረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን በመሆኑ ጉባኤውን ለማዘጋጀት የሚችል ብቃት

እንዳላቸው ሥራ አስፈጻሚው በሚገባ ተመልክቶ ስምንተኛው ጠቅላላ ጉባኤ ደብረ ምህረት ቅዱስ ሚካኤል ዋሺንግተን ዲሲ እንዲካሄድ ወስኗል።

- የስምንተኛው ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ ሊኖረው ስለሚገባ የመርሃግብር ይዘት ቅደመ ዝግጅት ተዘጋጅቷል።
- የማህበራችን በጎ አድራጎት ክፍል ባለፉት የስራ ዘመናት ዘለቄታዊ የሆነ የልማት ፕሮጀክት ከማህበረ ቅዱሳን በመውሰድ ስራውን እየሰራ እንደነበረ ባሳለፍነው የሪፖርት ወራት ተጠቅሶ ይገኛል። በዚህ የስድስት ወር ጊዜ ውስጥም ተጀምሮ የነበረ ሥራ ተጠናቆና ርክክብ ተደርጎ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል። ለዚህም ስራ ማስኬጃ ከማህበሩ ካዝና 1600 ዶላር ወጪ ተደርጓል።
- የማበህሩ በጎ አድራጎት ክፍል ከዚህ ቀደም ከተሰሩት ሥራዎች በተጨማሪ በዚህ ዓመት ዘለቄታዊና ግዚያዊ ርዳታ የሚያስፈልጋቸው አድባራትና ገዳማትን በመለየት ለዚሁ ሥራ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ ሰንበት ትምህርት ቤቶችን በማነጋገር አጥጋቢ መልስ ተገኝቷል።
- የአባልነት መመዝገቢያ ቅጽ በማህበራችን ግንኙት ክፍል ተዘጋጅቶ ቀርቧል።
- የማህበሩ አባላት አጠቃላይ በሰሜን አሜሪካ የሚገኙ የአብያተክርስቲያናት ሰንበት ትምህርት ቤቶች አገልጋዮች እንደሆኑ ይታወቃል።
- ወርሃዊ ክፍያ በተመለከተ ከዚህ ቀደም ይደረግ የነበረው እንቅስቃሴ አናሳ በመሆኑ የማህበራችን ሂሳብ ክፍል አባላቱ ወርሃዊ ክፍያቸውን በቀላሉ መንገድ እንዲከፍሉ ሊያደርግ የሚያስችል አሰራር በመንደፍ የቅስቀሳ ስራ እየሰራ ይገኛል።
- የማህበራችን የመዝሙር ክፍል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የበዓላትን አከባበር የሚያሳይ አንድ ዲቪዲ ካሴት ለማዘጋጀት በሚደረገው ጥረት መዝሙራትን የማሰባሰቡ ስራ ሰባ በመቶ ተጠናቋል።እንደዚሁም የቅዱስ ያሬድን ታሪክ የሚወሳ አንድ መድብል ለማዘጋጀት ዝግጅት ተደርጓል።
- ማህበሩ ከዚህ ቀደም ለሰባት ዓመታት ጉባኤ ሲያካሂድ ጉባኤውን የሚያወሱ የተቀረጹ ዲቪዲዎች በማህበሩ እጅ ተይዘው ይገኛሉ። እነዚህን ታሪካዊ ይዘት ያላቸው ዲቪዲዎች በማሰባሰብ እና በጥራት በማዘጋጀት ለሽያጭ የሚውልበት መንገድ ከማዘጋጀት አንጻር ዲቪዲዎችን የማሰባሰብ ስራ እየተሰራ ይገኛል።

## ፪ ባለፈው ስድስት ወራት ታቅደው ሳይከናወኑ የቀሩ ሥራዎች

መንፈሳዊ ስራዎች ሁል ግዜ አልጋ በአልጋ አይነት ጉዞ የሚኬድበት ሳይሆን ብዙ መሰናክል የበዛበት በእሾኽና በአሜከላ የታጠረ እንደሆነ ይታወቀል።ስለሆነም ቅዱስ ጳውሎስ ሃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን አችላለሁ እንዳለ በዕቅዳችን የታቀዱ ነገር ግን ሳይሰሩ ቀሩትን አንዳንድ ሥራዎች ለማቅረብ እንሞክራለን።

- በዚህ ስድስት ወራት የማህበራችን ትምህርት ክፍል አባላት በገጠማቸው የትምህርትና የስራ ጫና ምክንያት ክፍሉ የሚጠበቅበትን ወቅታዊ የሆኑና በአበይት በዓላትን የሚያወሱ ትምህርቶች በወቀቱ ማቅረብ አልቻሉም።
- የማህበራችን ዌብሳይት ከባለሞያ ዕገዛ ጥረት አንጻር ማስተላለፍ የሚገባውን ያህል መልዕክት ባለማስተላለፉ በአባላት ዘንድ ዌብ ሳይቱ ተከፍቶ የመታየቱ ዕድሉ ሌሎች ዌብ ሳይት ካላቸው አቻ ማህበራት ጋር ሲነጻጸር በጣም አናሳ ሆኖ ተገኝቷል።
- ማህበሩ የራሱን አባላት መዝግቦ ለመያዝ ከዚህ ቀደም ይጠቀምበት የነበረው የዳታ አያያዝ ሥርዓት ያልተሟላ ከመሆኑ የተነሳ ምን ያህል አባላት እንዳሉና ወርሃዊ ክፍያን በተመለከተ የሚከፍለውንና የማይከፍለውን ለይቶ ለማወቅ አልተቻለም።
- ማህበራችን አንድ ወጥ የሆነ አሠራር ለመስራት ሲነሳ ወይም መረጃ ለማግኘት በሚያስብበት ወቅት የመገናኛ መንገዶቹ ጠባብ እንደመሆናቸው መጠን የሚፈለገውን ያህል መረጃ በተፈለገው የግዜ ገደብ ውስጥ አለማግኘት።
- አባላቱ ስለማህበሩ ያላቸው ግንዛቤ አንድ ወጥ ባለመሆኑ አጠቃላይ ስራዎችን ለማከፋፈል እንደ አንድ አቢይ ችግር ሆኖ የታየ ጉዳይ ሆኖ መገኘቱ

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ማህበራችን በዚህ ስድስት ወራት በዕቅድ ተይዘው ነገር ግን ሳይተገበሩ የቀሩ አቢይ ስራዎች ናቸው፡፡ስለሆነም ሳይከናኑ በቀሩት ዕቅዶች ላይ **የተሰጡ የመፍትሄ ሃሳቦች**

- የማህበራችን ትምህርት ክፍል አባላት በትጋት እንዲሰሩና፣ አጋዥ የሚሆኑ አባላት እንዲመደቡላቸውና ለትምህርት የሚያገለግሉ ጽሁፎች በማዘጋጀት ሊረዱ ከሚችሉ አካላት ጋር ጠንከር ያለ ግንኙነት መፍጠር
- የማህበሩ ዌብሳይት በሞያቸው አስፈላጊ የሆነ መረጃና የማህበሩን እንቅስቃሴ በየጊዜው ሊያስረዳ ይችል ዘንድ ሊያገለግሉ የሚችሉ ሰንበት ተማሪዎችን ከየአጥቢያዎች በማሰባሰብ አንድ ኮሚቴ ማዋቀር
- ማህበሩ አባላቱን መዝግቦ የሚይዝበት አሰራር በመቀየር አባላት የሚመዘግብበትን መንገድ አጋዥ ከሆኑ አባላት ጋር በመቀናጀት መስራት
- ስለማህበሩ ግንዛቤና በቂ ዕውቀት የሌላቸውን በሰሜን አሜሪካ አብያተክርስተደናት ውስጥ የሚገኙ ሰንበት ተማሪዎች በተመለከተ የማህበሩ ሥራ አስፈጻሚዎች ከተለያዩ አካባቢ የተሰባሰቡ እንደመሆናቸው መጠን በሚያገለግሉበት ሰንበት ት/ቤቶች ስለማህበሩ እንቅስቃሴና ስራዎች ከሰንበት ትምህርት ቤቶች ስራ አስፈጻሚዎች ጋር በመነጋገር ፕሮግራም በመያዝ የጋራ ውይይት መፍጠርና ግንዛቤን ማሳደግ

በቀሪው ስድስት ወር መሰራት የሚገባቸውን ዕቅዶች ተግባራዊ ለማድረግ እንችል ዘንድ እግዚአብሔር አምላካችን እንዲረዳን በምክር በሐሳብ እና በጸሎት እንድታስቡን እንጠይቃለን፡፡